# ፀረ-ሙስና

ፀረ-ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 36 የካቲት 30/2018 ዓ.ም


## በውስጥ ገፆች


ኢትዮጵያና አዘርባጃን በፀረ-ሙስና ሙስና ትግል የመግባቢያ ሰነድ ተፈራረሙ

ገጽ 2

የነገ ሀገር ተረካቢ ታማኝና በእውቀት የታነጸ ሥነምግባራዊ ትውልድ የሚፈጠረው በትምህርት ቤቶች ነው

ገጽ 4

ዲጂታል የሀብት ምዝገባ ሙስናን የሚከላከል ዘመናዊ መሳሪያ

ገጽ 6


## በመዲናዋ የአገልግሎት አሰጣጥን በቴክኖሎጂ ከማዘመን ሥራ ጎን ለጎን፣ ተገልጋዮችን በሚያንገላቱና ብልሹ አሰራር በሚፈጽሙ አካላት ላይ ጠንካራ የተጠያቂነት እርምጃ እየተወሰደ ነው ተባለ

በአዲስ አበባ ከተማ ለረጅም ዓመታት መሰረታዊ የህዝብ ጥያቄ ሆነዉ ከቆዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች አንዱ የመንግስት ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ፣ ግልጽ እና ከብልሹ አሰራሮች የጸዳ አለመሆኑ ነዉ:: አገልግሎት ለመስጠት ጉቦ መጠየቅ፣ የቅንነት መጓደል፣ ተገልጋዮችን ማንገላታት እና መሰል የአገልግሎት አሰጣጥ ክፍተቶች ህብረተሰቡ ከመንግስት ተቋማት የሚፈልገዉ አገልግሎት እንዳያገኝ ትልቅ ማነቆ ሆነዉ ቆይተዋል:: የከተማ አስተዳደሩም የአገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል እና የተቋም ግንባታን በማጠናከር



በዘርፉ የሚታየዉን ውስንነት ለመቅረፍ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ላይ ይገኛል:: በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት መስጠት፣ የሰው ኃይል ሥነምግባርን ማሻሻል፣ ግልፅ እና ቀልጣፋ አሰራርን መተግበር የከተማ አስተዳደሩ ዋነኛ የትኩረት ማዕከሎች ናቸዉ:: የከተማ አስተዳደሩ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቱን ዲጂታላይዝ ለማድረግ በሰራው ጠንካራ እና ተከታታይ ስራ እስካሁን 370 አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ ታግዘው አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ችሏል::ሁለት አዳዲስ "መሶብ" የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት መስጫዎች ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲለሙ በማድረግ ወደ አገልግሎት የገቡ ሲሆን፣ የተለያዩ አገልግሎቶችን በተቀናጀ መንገድ በመስጠት ላይ ይገኛሉ:: በተሰራዉ ስራም የነዋሪዎችን ቅሬታ፣ የተገልጋዩን እንግልት፣ ጊዜንና ወጪን በመቀነስ ጥራት ያለው አገልግሎት በመስጠት የተገልጋይን እርካታ በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ ተችሏል:: ያልተቀረፉ የአገልግሎት አሰጣጥ ማነቆዎችን ለመቅረፍም


ወደ ገጽ 2 የዞረ...


## ክቡር ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ፒኤችዲ) በኢትዮጵያ ከህንድ አምባሳደር ጋር በፀረ-ሙስና ትግል ማጎልበትና ትብብር ሥራዎች ላይ ውይይት አደረጉ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ፒኤችዲ) በኢትዮጵያ ከህንድ አምባሳደር ጋር በፀረ-ሙስና ትግል ማጎልበትና ትብብር ሥራዎች ላይ ውይይት አድርገዋል:: በውይይቱ በኢትዮጵያ የህንድ ኢንቨስተሮች የቢዝነስ ከባቢ ምቹ እና የተቋማት አገልግሎት አሰጣጥን ከሙስና የፀዳ ከማድረግ አንጻር ያለውን ምልከታ የጋራ ማድረግ



ተችሏል:: በሌላ በኩል የፀረ-ሙስና ትግልን ከማጠናከር አንጻር በሁለቱ አገሮች መካከል ትብብር የሚያስፈልግ በመሆኑ፣ በወሳኝ ጉዳዮች ላይ የጋራ የመግባቢያ ስምምነቶች መዘጋጀት እንዳለባቸው ተመላክቷል::

ትውልድን በሥነምግባር፤ ተቋምን በአሰራር!

የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካልዎት NCRS ሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም ባሉበት ሆነው ይጠቁሙ!

## ከገጽ 1 የዞረ

ተጨማሪ ተቋማትንና አገልግሎቶችን ወደ ማዕከላቱ የማስገባት ስራ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል፡፡ አገልግሎቱን ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግም በዘጠኝ ክፍለ ከተሞች ደረጃቸውን የጠበቁ የመሶብ ማዕከላት በመገንባት ላይ ያሉ ሲሆን፣ በቅርቡ ወደ አገልግሎት ይገባሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ የከተማ አስተዳደሩ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማዘመን ከሚያደርገዉ ጥረት በተጨማሪ ተገልጋዮችን በማንገላታትና፣



ተገቢ ያልሆነ ጥያቄ በመጠየቅ የተለያዩ ጥፋቶችን የፈፀሙ አካላትንም ተጠያቂ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ተጠያቂነት ከማስፈን አንፃር በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ብቻ 61 አመራሮች፣ 126 ዳይሬክተር እና ቡድን መሪዎች እንዲሁም 3 ሺህ 542 ሰራተኞች በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ በፈፀሙት ጥፋት ተጠያቂ መደረጋቸዉን ክብርት ከንቲባ አዳነች አቤቤ ለምክር ቤት አባላት ባቀረቡት የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ አንስተዋል፡፡ ተገልጋዮች በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲኖራቸውና የድርሻቸውን ኃላፊነት መወጣት እንዲችሉም እየተሰራ ይገኛል፡፡ የመማክርት ጉባኤዎች በየደረጃዉ ተቋቁመዉ ወደ ተግባር የገቡ ሲሆን፣ የመዲናዋ ነዋሪዎች በእንጠያየቅ መድረኮች ጥያቄያቸውን አንስተው በአመራሩ ምላሽ እንዲሰጣቸው **በመደረግ ላይ ነው፡፡**

## የኮሚሽኑ ሴት የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ለሰሊሆም የአዕምሮ ህሙማን መርጃ ማህበር ድጋፍ አደረጉ




የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሴት የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ዓለም ዓቀፍ የሴቶች ቀን (ማርች 8 ምክንያት በማድረግ ለሰሊሆም የአዕምሮ ህሙማን መርጃ ማህበር የአልባሳት ድጋፍ አድርገዋል፡

፡ ዓለም ዓቀፍ የሴቶች ቀን (ማርች 8) በየአመቱ በተለያዩ ሁነቶች የሚከበር ሲሆን፣ ዘንድሮም ‹‹50 ዓመታት የሴቶች ድምጽ ለእኩልነትና ለበለጸገች ኢትዮጵያ›› በሚል መሪ ቃል ተከብሮ ውሏል፡፡ የኮሚሽኑ ሴት የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞችም በዓለም አቀፍ የሴቶችን ቀን ምክንያት በማድረግ ለሰሊሆም የአዕምሮ ህሙማን መርጃ ማህበር የአልባሳት ድጋፍ ያደረጉት ሲሆን፥ የማህበሩን የአረጋዊያንና ህጻናት መርጃ መዓከልን ተዘዋውረው ጎብኝተዋል፡፡ በተጨማሪም በዓሉን ምክንያት በማድረግ ከአቢሪ ጤና ጣቢያ ጋር በመተባበር በጤና ነክ ጉዳዮች የግንዛቤ ማስጨበጫ በጣቢያው በባለሙያዎች ተሰጥቷል፡፡ የተሰጠውን ግንዛቤ ማስጨበጫ መነሻ በማድረግ ለኮሚሽኑ ሴት የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች የጤና ምርመራ ተደርጓል፡፡

## ኢትዮጵያና አዘርባጃን በፀረ-ሙስና ሙስና ትግል የመግባቢያ ሰነድ ተፈራረሙ





በኢትዮጵያና በአዘርባጃን መካከል ያለውን የሁለትዮሽ ግንኙነት ይበልጥ ለማጠናከር የሚያስችልና በፀረ-ሙስና ትግል ላይ ያተኮረ ታሪካዊ የመግባቢያ ሰነድ ተፈርሟል፡፡

ይህ ስምምነት ሁለቱ አገራት በፀረ-ሙስና እና የተቋማት አቅም ግንባታ ላይ በጋራ እንዲሰሩ መንገድ ይከፍታል፡፡ አዘርባጃን በተለይም በመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ እና በዲጂታል አሰራር ሙስናን በመቀነስ ረገድ ያላትን ዓለም አቀፍ ተሞክሮ ለኢትዮጵያ ለማካፈል ዝግጁ መሆኗ ተገልጿል፡፡ ይህም የኢትዮጵያን የፀረ-ሙስና ተቋማት የመከላከል አቅም ወደ ላቀ ደረጃ ያሸጋግረዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የስምምነቱ አንዱና ዋናው ፋይዳ ግልጽነት የሰፈነበት የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት መገንባት ነው፡፡ ይህም ለባለሀብቶች ከሙስና የጸዳና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ ዜጎች የመንግሥት ተቋማት አሰራር ግልጽና ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲሆን በማድረግ ፍትሃዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላል፡፡

በአጠቃላይ ይህ የተፈረመው ስምምነት ኢትዮጵያ ሙስናን ለመዋጋትና ለዜጎቿ የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት የጀመረችውን ጉዞ የሚያፋጥን ስትራቴጂካዊ እርምጃ መሆኑ ተመላክቷል፡፡

## ተቋማዊ አሰራርን ለማጠናከር የድጋፍና ክትትል ሥራ ወሳኝ መሆኑ ተመላከተ



የሲዳማ ክልል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የ2018 በጀት ዓመት የእስካሁን የተግባር አፈፃፀም ግምገማ እና የድጋፍና ክትትል ግብረ-መልስ የምክክር መድረክ አካሄዷል፡፡ በመድረኩ ላይ የክልሉን የፀረ-ሙስና ትግል የሚያጠናክሩ ቁልፍ ስኬቶችና የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች ተመላክተዋል፡፡

በመድረኩ የተገኙት የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ክብርት ወ/ሮ ዘላለም ለማ ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ በተደረገ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራ ከ32 ሚሊዮን ብር በላይ የመንግስትና የሕዝብ ሀብት ከምዝበራ ማዳን ተችሏል ብለዋል፡፡ ከገንዘብ ማዳን ሥራው ባሻገር፣ በሀብት ምዝገባና በትውልድ ሥነ ምግባር ግንባታ ላይ ያከናወናቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች አበረታች ውጤት እያስመዘገቡ መሆኑንም ክብርት ኮሚሽነሯ ገልጸዋል፡፡

ተቋማዊ አሰራርን ለማጠናከር ቀጣይነት ያለው የድጋፍና ክትትል ሥራ ወሳኝ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡ ክብርት ኮሚሽነሯ አክለውም ክፍተቶችን እንደ ግብዓት በመያዝ እና ጠንካራ ጎኖችን በማስቀጠል፣ የታዩ ጉድለቶችን በፍጥነት የዕቅዳችን አካል አድርገን መስራት ይኖርብናል ሲሉ አሳስበዋል፡፡ በዕለቱ የ2018 በጀት ዓመት የሁለተኛ ሩብ ዓመት የድጋፍና ክትትል ግብረ-መልስ ሪፖርትና የስድስት ወር ስራ አፈፃፀም ሪፖርት ቀርቧል፡፡ በሪፖርቱም በሩብ ዓመቱ የታዩ ዋና ዋና ስኬቶችና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች በዝርዝር ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

ተሳታፊዎች በበኩላቸው በቀረበው ሪፖርት ላይ ሰፊ ውይይት ካደረጉ በኋላ፣ በቀጣይ የታዩ ክፍተቶችን በማረም እና የሙስና መከላከል ስራዎችን ይበልጥ በማጠናከር ውጤታማ ሥራ ለመሥራት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ በመድረኩ ላይ ከክልልና ከአራቱም ዞን የተወጣጡ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ዳይሬክተሮችና ዴስክ ኃላፊዎች ተገኝተዋል፡፡



## ጠንካራ ሰራዊት በመሣሪያ ብቻ ሳይሆን በሥነ-ምግባር እና በሀገር ፍቅር ይገነባል - ክብርት ማርታ ሉዊጂ





የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን "የከፍተኛ አመራሩ አርዓያነት፣ ለፀረ-ሙስና ትግሉ ያለው ፋይዳ" በሚል መሪ ቃል ከመከላከያ ዘርፍ ከፍተኛ አመራሮች ጋር ስልጠናዊ ውይይት አካሄደ፡፡ በውይይቱ ላይ የተገኙት የመከላከያ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ክብርት ማርታ ሉዊጂ ጠንካራ ሰራዊት በመሣሪያ ኃይል ብቻ ሳይሆን በሥነ-ምግባር፣ በታማኝነት እና በሀገር ፍቅር ላይ እንደሚመሰረት ገልጸዋል፡፡

ተቋሙ የተጣለበትን አገራዊ ተልዕኮ በኃላፊነትና በብቃት መወጣት የሚችለው መልካም ሥነ-ምግባርን የተላበሰና ዲሲፕሊኑን የጠበቀ ሰራዊት ሲገነባ ነው ብለዋል፡፡ ሚኒስትር ዴኤታዋ አክለውም በማንኛውም ግዳጅ ወቅት የላቀ አፈጻጸም ለማስመዝገብ የሚያጋጥሙ የጥቅም ግጭቶችን በሕግና አሠራር መፍታት እንዲሁም የሀገርን ጥቅም ማስቀደም እንደሚገባም አሳስበዋል፡፡ ሙስና የሀገርን ልማትና ዕድገት የሚያደናቅፍ "የፊት ለፊት ተዋጊ ፀረ-ሕዝብ" መሆኑን የጠቀሱት ክብርት ማርታ ሎጂ፤ ሰራዊቱ ይህንን ጠላት በሕጋዊ የመታገያ መስመር በቁርጠኝነት እየታገለው እንደሚገኝ በንግግራቸው አረጋግጠዋል፡፡

የኮሚሽኑ የሥነምግባር ግንባታ ዘርፍ ም/ ኮሚሽነር ክቡር አቶ ፍቃዱ ሰቦቃ በበኩላቸው ሙስና የአመለካከት እና አስተሳሰብ ዝቅጠት ውጤት የሆነ፣ ሀገር አፍራሽና የእሴቶቻችን ፀር ነው ብለዋል፡፡ ሙስናን ለመከላከል የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ቢሆንም ኮሚሽኑ በዋናነት ባለቤት ሆኖ የሥነምግባር ግንባታ እና የቅድመ መከላከል ስራዎችን እየሰራ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡ ይህ ግምገማዊ ስልጠና ልምድ የምንለዋወጥበት፣ በዘርፉ የሚስተዋሉ የጥቅም ግጭትን ማስተዳደር የሚችል አመራር ለመፍጠር፣ ብልሹ አሰራሮች እንዳይፈጠሩ በጋራ የምንታገልበትና የአስተሳሰብ ለውጥን የምንፈጥርበት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በሥልጠናዊ ውይይቱ በዘርፉ የሚስተዋሉ ዋና ዋና የሙስና ሥጋት እና ተጋላጭነት መገለጫ የሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ቀርበው ሰፊ ውይይት የተደረገባቸው ሲሆን፤ ከተሳታፊዎች ጥያቄዎች፣ ሀሳብና አስተያየቶች ተነስተው ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ መድረኩ የሀገር ፍቅርን፣ ታማኝነትን፣ ሥነምግባራዊነትን፣ የህግ የበላይነትን የሚያከብር፣ ግልፀነት እና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን፣ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን የሚጠየፍ እንዲሁም ቁርጠኛ አመራርነት የሚፈጠርበት መሆኑን ተሳታፊዎች ገልፀዋል፡፡

# የከተማ መሠረተ-ልማቶችን ውጤታማ ለማድረግ ሙስናን በጋራ ልንታገል ይገባል - ክብርት ወ/ሮ ጫል ቱሳኒ



ኮሚሽኑ “የከፍተኛ አመራሩ አርዓያነት፤ ለፀረ-ሙስና ትግል ያለው ሚና” በሚል መሪ ቃል በሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥና የጥቅም ግጭትን ላይ ያተኮረ ስልጠናዊ ውይይት ከከተማና መሠረተ-ልማት ዘርፍ ከፍተኛ አመራሮች ጋር ውይይት አድርጓል፡፡

በስልጠና መድረኩ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የከተማና መሠረተ-ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ክብርት ወ/ሮ ጫልቱ ሳኒ ሙስናን መታገል የመንግስት አቅጣጫ በመሆኑ በየደረጃው ያለ አመራር ትኩረት በመስጠት መስራት አለበት ብለዋል፡፡ ችግሩን ለመቅረፍም ይህን መሰል ሥልጠና በየጊዜው በመስጠት የአመለካከት ለውጥ ማምጣት እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

ሚኒስትሯ አክለውም የከተማና መሠረተ-ልማት ዘርፍ በባህሪው ካለው ስፋትና ሀብት አንጻር ለብልሹ አሠራር ተጋላጭ በመሆኑ አመራሩ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተጠንቅቆ መስራት እንዳለበት አሳስበዋል፡፡ በተለይ የከተማልማትና መሠረተ-ልማቶችን ውጤታማ ለማድረግ ሙስናን በጋራ ልንታገል ይገባል፡፡ ‹‹አሁን በየከተሞች የሚከናወነው የኮሪደር ልማት ውጤታማ ያደረግነው ሙስናን በመታገላችን ነው›› ብለዋል፡፡

የኮሚሽኑ የሥነምግባር ግንባታ ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ክቡር ፍቃዱ በበኩላቸው ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን ካስቀመጧቸው አምስቱ የመቀነስ ግቦች አንዱ ሙስናን መቀነስ ነው፡፡ በየደረጃው ያሉ አመራሮች ለሙስና እና ብልሹ አሰራር እንዳይጋለጡ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ መጠንቀቅ አለባቸው ብለዋል፡፡ ም/ኮሚሽነሩ አክለውም የሙስና ዋነኛው መንስኤ የአመለካከት ዝቅጠትና የማህበራዊ እሴቶች መሸርሸር መሆኑን ገልፀው፤ ሁሉም አካላት በትውልድ ሥነምግባር ግንባታ ላይ በቅንጅት መስራት እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

በስልጠና መድረኩ ተሳታፊዎች የተለያዩ ጥያቄዎች፣ ሀሳቦችና አስተያየቶችን አንስተው ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በስልጠናው የከተማና መሠረተ-ልማት ሚኒስቴር ከፍተኛ አመራሮች፣ የተጠሪ ተቋማት አመራሮችና የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም የክልልና ከተማ አስተዳደር



# ለመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ዘርፍ ከፍተኛ አመራሮች በጥቅም ግጭት መከላከል ዙሪያ ስልጠና ተሰጠ




የፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር በጋራ በመሆን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፍተኛ አመራሮች ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና የጥቅም ግጭት መከላከልና ማስተዳደር በሚል ርዕስ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በመድረኩ የተገኙት የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ሚኒስትር ክቡር አብርሃም በላይ (ዶ/ር) ይህ መድረክ በዋናነት ከሥነ-ምግባርና ከዲሲፕሊን ጋር ተያይዞ ክፍተቶች ካሉ ለማረም እና ለማስተካከል እንዲሁም ጥሩ ተሞክሮዎችን ካሉ ለመማር የሚያስችል ስለሆነ ሥልጠናው ለተቋማችን አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡ ይህ ተቋም ሰፊ የመንግስት ሀብት እና ብዙ ፕሮጀክቶችን የሚያንቀሳቅስ እንደመሆኑ መጠን ለስራው ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ እንዲያስችል ተናግረዋል፡፡ የሀገርን ብልጽግና ማረጋገጥ የሚቻለው ሥራን በዲሲፕሊን ሲመራ እና የተመደበው በጀት ለታለመለት ዓላማ ሲውል ብቻ መሆኑን ጠቅሰው፣ በጀት በየመስመሩ እየተቆራረጠ ሌባ እየበላው ከሄደ ልማትም፣ እድገትም ይቀጭጫል ብለዋል፡፡

የሚገባውን ለማይገባው የመስጠት ጉዳይ የግለሰብ አመለካከት ጉዳይ ነው ያሉት ሚስትሩ ሰው አመለካከቱ ካልተቀየረ የፈለገ ስርዓት ብንዘረጋ ከመስረቅ ወደ ኋላ አይልም፡፡ ለዚህም አሰራርን ዲጂታላይዝ በማድረግ መፍትሄ እንሰጣለን ስንል ስራን እንዲያግዝ ካልሆነ በስተቀር አመለካከቱ ያልተቀየረ ሰው ከሌቦች ጋር በመመሳጠር ዲጂታል ግኝን በመቀየር የጥቅም አጋሮቹን ሊያስተሳስር ይችላል ሲሉ ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም እኛም እንደ ተቋም ወቅታዊ እና የተሻሻለ መረጃ ለኮሚሽኑ ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ በጥናት ተለይተው የተሰጡ ምክረ-ሀሳቦችን ተቀብሎ መተግበር ለተቋሙ ያስፈልጋል፡፡ ህመማችን ፕሮጀክት አለመጨረስ ነበር አሁን ላይ በተያዘላቸው ጊዜና በጀት እንዲጠናቀቁ በትጋት እየሰራን እንገኛለን፤ በርካታ ፕሮጀክቶችም ተጠናቀዋል፡፡ ፕሮጀክት አቋርጠው የሚወጡ ኮንትራክተሮች አሉ ካልን አቋርጠው እንዲወጡ የሚያስገድዷቸውን ችግሮችን ጭምር ማየት ተገቢ ነው ብለዋል፡፡

ስለዚህ ፕሮጀክቶች እንዳይቋረጡ ከተፈለገ አስፈላጊውን ድጋፍ አድርጎ ክፍተት ካለ ተጠያቂ ማድረግ ይቻላል፡፡ የመንግስት የልማት ድርጅት ስለሆኑ ብለን ተጠያቂ ያላደረግነው ኢንተርፕራዝ የለም፡፡ በዚህ ዙሪያ ጨከን ያሉ ውሳኔዎችን በማሳረፍ እንዲስተካከሉ የማድረግ ስራ ሰርተናል ሲሉም አክለዋል፡፡

የፌደራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና መከላከል ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ክቡር እሸቴ አስፋው በበኩላቸው ሁሉም የመንግስት ተቋማት፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ህዝባዊ ድርጅቶችም የፀረ-ሙስና ትግሉ ባለቤት መሆን ይገባቸዋል ብለን ለመንግስት ባቀረብነው ጥያቄ መሰረት የፀረ-ሙስና ጉዳይ ትልቅ ሀገራዊ አጀንዳ እንዲሆን ክቡር ጠቅላይ ሚኒስተር አቅጣጫ አስቀምጠዋል ሲሉ ገልፀዋል፡፡

ም/ኮሚሽነሩ አክለውም መንግስት ካስቀመጣቸው ቁልፍ አጀንዳዎች ውስጥ አምስቱ የመቀነስ ግቦች ውስጥ አንዱ በሁለተኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠው ሙስናን መቀነስ ነው፡፡ ይህም በተቋማት ለምንሰራው የሥነ-ምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ስራ ከፍ እንዲል አድርጎታል ብለዋል፡፡ እንደ መስኖ እና ቆላማ ሚኒስቴር የጥቅም ግጭት ሊከሰትባቸው የሚችሉ የመስኖ ፕሮጀክቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ እሱን በአግባቡ በመከላከልና በማስተዳደር ፕሮጀክቶች ከጥቅም ግጭት ነጻ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡



# ሙስና መረጃው ድብቅ፣ የምርመራ ሥራውም ረቂቅ ነው





የአማራ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሙስና እና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል ከክልሉ ፖሊስ ዋና ጠቅላይ መምሪያ እና ፍትሕ ቢሮ ጋር በቅንጅት በሚከናወኑ ሥራዎች ላይ ውይይት አድርጓል፡፡

የአማራ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሀብታሙ ሞገስ እንደ ኮሚሽን ሙስና እና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ትውልድ ለመገንባት በትኩረት እየተሠራ መኾኑን ተናግረዋል፡፡ የሙስና ብልሹ አሠራር እንደሀገር እና እንደ ክልል እንደ አንድ የተለየ ችግር መኾኑን ተናግረዋል፡፡ ችግሩን ለመፍታት ደግሞ መንግሥት አሳሳቢነቱን ተረድቶ የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ እንደሚገኝ ነው የጠቀሱት፡፡ በማሳያነትም ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የተቋማትን አሠራር ዲጂታላይዝድ የማድረግ ሥራ እየተሠራ መኾኑን አንስተዋል፡፡ በየአካባቢው ተቋማት መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ሥራ እንዲጀምሩ መደረጉንም አንስተዋል፡፡

ኮሚሽኑ ደግሞ ከብዙ አካላት ጋር ተቀናጅቶ እየሠራ እንደሚገኝ ነው የገለጹት፡፡ ከፖሊስ እና ፍትሕ አካላት ጋር የሀብት ምዝገባ እና ማጣራት፣ የአሠራር ጥናት እና አስቸኳይ ሙስና መከላከል፣ ጥቆማዎች ሲመጡም ለሚመለከተው አካል በመላክ በኩል ተቀናጅተው እየሠሩ እንደኾነ ተናግረዋል፡፡ ሦሥቱ ተቋማት ተቀናጅተው በመሥራታቸው ከጅምር ባለፈ አመርቂ ውጤት መጥቷል ተብሎ እንደማይታሰብም ጠቅሰዋል፡፡ በጅምር ደረጃ በተሠሩ ሥራዎች ወንጀለኞች ተጠያቂ እንዲኾኑ የማድረግ፣ ተቋማት ለብልሹ አሠራር እና ሙስና የተጋለጡ አሠራራቸውን እንዲያስተካክሉ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል ብለዋል፡፡

ሙስና እና ብልሹ አሠራርን በዋናነት ለመከላከል ተቋማት መረጃዎችን የመለዋወጥ፣ በጋራ ማስረጃዎችን የማሰባሰብ፣ በጋራ ወንጀለኞችን ተጠያቂ የሚያደርጉ ሥራዎችን መሥራት በቀጣይ ትኩረት እንደሚሰጥባቸው ገልጸዋል፡፡ በየተቋማቱ የሚታዩ አሠራሮችን በጋራ የማጥራት ሥራዎችም ትኩረት እንደሚደረግባቸው አንስተዋል፡፡ የመንግሥት ሀብት ከመመዝበሩ በፊት መከላከል፣ ተመዝብሮ ሲገኝ ደግሞ ተገቢ ክትትል አድርጎ የማስመለስ ሥራ በቅንጅት እንደሚሠራም ጠቅሰዋል፡፡

የአማራ ክልል ፖሊስ ዋና ጠቅላይ መምሪያ ምክትል ኮሚሽነር እና የወንጀል ምርመራ ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ ምክትል ኮሚሽነር ታደሰ አያሌው ቀደም ሲል ከሙስና እና ብልሹ አሠራር ጋር ተያይዞ ቅንጅታዊ አሠራሮች ተግባራዊ ሲደረጉ መቆየታቸውን ተናግረዋል፡፡ ውይይቱ ከዚህ በፊት በነበረው አሠራር የሀብት ምዝገባ እና ማጣራት፣ ቅንጅታዊ አሠራር እና ከጥቆማ አሠጣጥ ጋር ተያይዞ ሲያጋጥሙ የነበሩ ችግሮችን ለማረም የተደረገ መኾኑን ነው የጠቀሱት፡፡

እንደ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያው ከዚህ በፊት ከመሬት ወረራ እና ከግዥ ሥርዓት ጋር ተያይዞ ይበልጥ በትኩረት ሲሠራ መቆየቱን አንስተዋል፡፡ በሚፈለገው ልክ ግን ውጤት መጥቷል ማለት እንደማይቻል ነው የጠቀሱት፡፡ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ክልሉ በጸጥታ ችግር መቆየቱ ብልሹ አሠራር እና ሙስናን በተገቢ ኹኔታ የመከላከል ተግባር ላይ ውስንነቶች እንዲኖሩ ያደርጋል ነው ያሉት፡፡

በውይይቱ ሲሳተፉ ያገኘናቸው የሰሜን ጎጃም ዞን ፍትሕ መምሪያ የዞን አቃቢ ሕግ እና የሙስና ወንጀል የሥራ ሂደት አስተባባሪ ጎይሌ ጥሩነህ የሙስና እና ብልሹ አሠራር ወንጀል መረጃው ድብቅ እና የምርመራ ሥራው ረቂቅ መኾኑን ተናግረዋል፡፡ የሙስና ወንጀል በባሕሪው ከመደበኛ ወንጀል እንደሚለይም አንስተዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ተቀናጅቶ መሥራት እና ውጤት ማምጣት ያስፈልጋል፤ በቀጣይም ከዚህ በፊት ከነበረው በተሻለ ተቀናጅተን እንሠራለን ብለዋል፡፡

## የከተማ መሠረተ-ልማቶችን ውጤታማ ለማድረግ ሙስናን በጋራ ልንታገል ይገባል - ክብርት ወ/ሮ ጫል ቱሳኒ





የፌዴራል ሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከትምህርት ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት ከፍተኛ አመራሮች ጋር ሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥና የጥቅም ግጭት ማስወገድና ማስተዳደር በሚል ርዕሰ ጉዳይ ላይ ዘርፍ-ተኮር ስልጠናዊ ውይይት አካሂዷል፡፡

በመድረኩ በአዲሱ የትምህርት ፍኖተ ካርታ የሥነምግባር ትምህርት ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ መሆኑን የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ክብርት ወ/ሮ አየለች እሸቴ በውይይቱ ተናግረዋል፡፡ ሥነምግባር ሙስናን ለመከላከልና ሥነምግባራዊ ውሳኔ ለመስጠት መሠረት ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ በትውልዱ ላይ እየሰሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

መንግሥት ትውልድ መቅረጽ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ በዚህም መሠረት የትምህርት ዘርፉ የትውልድን ሥነ-ምግባር ከመሠረቱ ለማነጽ የግብረገብ ትምህርትን በሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ አካትቶ እየሰጠ መሆኑን አንስተዋል፡፡ አክውም ‹‹ትምህርት ቤቶች የግብረገብ ትምህርትን በሥርዓተ-ትምህርቱ ውስጥ በማካተት፣ ተማሪዎችን በመልካም ሥነ-ምግባር በማነጽ ሙስናን ከሥር መሰረቱ ለመቅረፍ እየተሠራ ነው›› ብለዋል፡፡

ከሥነምግባር ግንባታ ባሻገር የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አመራር ስልጠናዊ ውይይቱ ከአመራሩ ዕለት ተዕለት ሥራ ጋራ ተያያዥነት ያለው መሆኑን ጠቅሰው፣ ውሳኔዎችን ስናሳልፍና ልዩ ልዩ ጉዳዮችን ስናስፈጽም ከጥቅም ግጭትና ከሙስና ተግባር የጸዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል ብለዋል፡፡ የሥነ-ምግባር ችግሮችን እና የሙስና ተግባራትን ለመከላከልና ለመቅረፍ አሰራሮችን ማዘመንና



ዲጂታላይዝ በማድረግ ለውጥ በሚያመጣ መንገድ በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን ጠቅሰው፣ ውይይታዊ ስልጠናውም ለእነዚህ ሥራዎች ውጤታማነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚበረክት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የኮሚሽኑ ሥነምግባር ግንባታ ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ክቡር ፍቃዱ ሰቦቃ የትምህርት ዘርፉ ከኮሚሽኑ ጋር በመተባበር የሙስና ተጋላጭነት ሂደቶችን በተጠናከረ ቅንጅት መከላከልና የፀረ-ሙስና ትግሉን በባለቤትነት መምራት የሚጠበቅበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ዘርፉ ትውልድን በማነጽ ላይ መሥራቱ ከኮሚሽኑ ጋር የሚያመሳስላቸው መሆኑን የገለጹት ም/ኮሚሽነሩ፣ በሥነ-ምግባር የታነጸ ትውልድ በመገንባት ሙስናን በመከላከል ረገድ ከፍተኛ ኃላፊነት የተጣለበት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

አመራሮች ውሳኔ በሚሰጡበት ወቅት በግል ጥቅምና በሕዝብ ጥቅም መካከል የሚፈጠረውን የጥቅም ግጭት በንቃት መለየትና ማስወገድ እንደሚገባቸው አጽንኦት ተሰጥቶበታል፡፡ የዕለቱ የውይይት መድረክ በሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ መስጠት ብቻ ሳይሆን የጥቅም ግጭት መከላከያ ስልቶችን ማለትም በምሳሌነት መምራት፣ የግል ፍላጎታቸውን ከተቋም ፍላጎት ጋር እንዳይጋጭ ማድረግ፣ የጥቅም ግጭት ለመከላከል የሚያስችል ፖሊሲና መመሪያ ማዘጋጀት፣ በየጊዜው የስልጠናና ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ማመቻቸት፣ የግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋት፣ ሙሉ ስብእናን መላበስና ፖሊሲና መመሪያ መሠረት በማድረግ አመራሩ ሊወስን እንደሚገባ ከተወያዮች የተነሱትን ጥያቄዎች አሰልጣኞቹ ማብራሪያ ሰጥተውበታል፡፡



## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የተሻለ ሥነምግባር ላስመዘገቡ ትምህርት ቤቶች እውቅና ሰጠ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያ መንፈቅ ዓመት በተማሪዎች ሥነ-ምግባር ላይ ተመስርቶ የተሻለ አፈጻጸም ላስመዘገቡ ትምህርት ቤቶች ዕውቅና ሰጥቷል፡፡ የዕውቅና ሥነስርዓቱ በአዲስ አበባ ከተማ የተከናወነ ሲሆን፤ የቢሮው ኃላፊ ዘላለም ሙላቱ (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ የምዘና ዕውቅናው ተቋማት ወደ ተሻለ የአፈጻጸም ደረጃ መሸጋገር እንዲችሉ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው፡፡



በክፍለ ከተማና ወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች እንዲሁም በሁሉም የመንግሥት 1ኛ እና 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና በሱፐርቪዥን ክላስተር ማዕከላት ላይ የተካሄደው ምዘና በተማሪዎች ሥነ-ምግባር ላይ ያተኮረ መሆኑን ገልጸው፤ በድምሩ 614 ተቋማት ተመዝነው የተሻለ ውጤት ላመጡት ዕውቅና መሰጠቱን ጠቁመዋል፡፡ ቢሮው ለትምህርት ዘርፉ ውጤታማነት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመሥራቱ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ መቻሉን ዘላለም (ዶ/ር) አስረድተዋል፡፡

ከዕውቅናው ባሻገር የድጋፍና ክትትል ሥራ መከናወኑን አስታውሰው፤ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ መንፈቅ ዓመት ዝቅተኛ አፈጻጸም ያሳዩ የትምህርት ተቋማት በቀጣይ ጠንክረው በመሥራት ለዕውቅና መብቃት እንደሚገባቸው አሳስበዋል፡፡

## የነገ ሀገር ተረካቢ ታማኝና በእውቀት የታነጸ ሥነምግባራዊ ትውልድ የሚፈጠረው በትምህርት ቤቶች ነው





የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በአሁኑ ሰዓት ለሀገር ኢኮኖሚ እና ለማህበራዊ ፍትህ ትልቅ እንቅፋት የሆነውን ሙስና እና ብልሹ አሰራር ለመቅረፍ በትውልድ ሥነምግባር ግንባታ ላይ ትኩረት ያደረገ ለት/ቤቶች የሥነምግባር ክበብ አስተባባሪ መምህራን የአሰልጣኞች ስልጠና ሰጥቷል፡፡

በስልጠናው የተገኙት የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ሀብታሙ ሞገስ የነገ ሀገር ተረካቢ ታማኝና በእውቀት የታነጸ ሥነምግባራዊ ትውልድ የሚፈጠረው በትምህርት ቤቶች ነው፡፡ ት/ቤቶች ደግሞ የትውልድን ቀጣይነት የሚያረጋግጡ በመሆኑ በልዩ ትኩረት መሥራቱ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡ አብዛኛው ህፃናትና ወጣቶች የሚገኙት በት/ቤቶች በመሆኑ በመልካም ሥነምግባርና በእውቀት የታነፀ ትውልድ ለመፍጠር የመምህራን ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ኃላፊነታችሁን ልትወጡ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል፡፡ የትውልዱን የሥነምግባር ስብራት ማስተካከል የምንችልበት ጊዜ አሁን ነዉ ያሉት ኮሚሽነሩ፣ ቀጣይ ክበቡን በማጠናከር ሁላችንም ተጋግዘንና ተባብረን የነገን ሀገር ተረካቢ ትዉልድ ልንፈጥር ይገባል በማለት ስልጠናዉን አስጀምረዋል፡፡

የኮሚሽኑ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስልጠና ባለሙያ ወ/ሮ በላይነሽ አሰፋ "ምሳሌያዊነት ያለዉ ሥነምግባራዊ የክበብ መሪነት" በሚል ርዕስ እና እንዴት የስልጠና ዝግጅት ማድረግ እንዳለባቸው ሰፋ ያለ ስልጠና ሰጥተዋል፡፡ የኮሚሽኑ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ጥናትና ምርምር ዳይሬክተር አቶ ገበየሁ ጥሩሰው በበኩላቸው የልጆችን ሥነምግባር ለመቀየር ከተፈለገ በመጀመሪያ ቅቡልነት ያለው ስብዕና ሊኖረን ይገባል፤ መምህርነት የሙያዎች ሁሉ እናት በመሆኑ ሙያችን ተጠቅመን አሁን ያለውን የሥነምግባር ስብራት በጋራ ተረባርበን ልናስተካክለው ይገባል ብለዋል፡፡

የትምህርት ቢሮው የሥነምግባር መኮንን አቶ ጉባይ የሥነምግባር ክበብ መመሪያ ከወጣ 6 ዓመት ሁኖታል፤ ነገር ግን እስካሁን መመሪያዉን ተጠቅመን በልጆች ሥነምግባር ላይ ያመጣነው ለውጥ ብዙም እንደማይታይ ጠቁመዋል፡፡ በት/ቤቶች የትውልዱን ሥነምግባር ይለውጣል ተብሎ የታመነበት ክበብ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ክበብ ነው፡፡ ቀጣይ በእውቀትና በሥነምግባር የታነፀ ሀገር ተረካቢ ትውልድ ለመፍጠር በክበቡ ላይ ሁላችንም በጋራ ትኩረት ሰጥተን ልንሰራበት ይገባል ብለዋል፡፡ የሥልጠና ተሳታፊዎች በአስተያየታቸው ኮሚሽኑ የትውልዱን ሥነምግባር ለማነፅ ይህንን መድረክ ማመቻቸቱ ሊመሰገን እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

## በአዲስ አበባ አዲስ ዲጂታል የነዋሪነት መታወቂያ መስጠት ተጀመረ

ላለፉት ዓመታት ሲያገለግል የነበረውን የወሳኝ ኩነትና የነዋሪነት አገልግሎት አሠራር በመቀየር፣ በፋይዳ ላይ የተመዘገቡ መረጃዎችን ያካተተ በአዲስና በዘመናዊ የዲጂታል ሲስተም የተዘጋጀውን የነዋሪነት መታወቂያ ካርድ መስጠት መጀመሩን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ አስታውቋል፡፡ ይህ አዲስ የተቀናጀ የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ሥርዓትም ፈጣን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችልና ከብልሹ አሠራር የፀዳ መሆኑ ተነግሯል፡፡

በተጨማሪም አዲሱ የነዋሪነት መታወቂያ ከ2015 ዓ.ም አካባቢ ጀምሮ አገልግሎት ላይ ከነበረው የነዋሪነት መታወቂያ አዳዲስ ገጽታዎችንና ይዘቶችን የሚያካትት መሆኑን የኤጀንሲው ምክትል ዋና ዳይሬክተርና የኩነትና ነዋሪዎች አገልግሎት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ጥጋቡ ሹመይ ገልጸዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም በ89 ወረዳዎች ላይ አዲሱን የነዋሪነት መታወቂያ አትሞ የማሠራጨት ሥራ እየተከናወነ እንደሚገኝ የተናገሩት ኃላፊው፤ ኤጀንሲው ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ ተቋማዊ ሪፎርም እያደረገ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

በሌላ በኩል ከሦስት ዓመት በፊት ጀምሮ የወረቀት መታወቂያን ወደ ዲጂታል መቀየሩን ያስታወሱት አቶ ጥጋቡ፤ በአሁኑ ወቅት ደግሞ የተወሰነ ማሻሻያ መደረጉን ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ነባሩ መታወቂያ በአንድ ጊዜ እንደማይቋረጥና ነገር ግን ቀስ በቀስ ከአገልግሎት እየወጣ በአዲሱ መታወቂያ እንደሚተካ አክለዋል፡፡ ስለሆነም እስካሁን ባለው ሒደት ሁለት ሺሕ የሚጠጉ የከተማዋ ነዋሪዎች አዲሱን መታወቂያ የወሰዱ ሲሆን፤ ለዚህ አገልግሎት የሚሆኑ አዳዲስ ፕሪንተሮች በግዥ ሒደት ላይ በመሆናቸው፣ ፕሪንተሮቹ ሲገቡ በ11ዱም ክፍለ ከተማ ቶሎ ተደራሽ እንደሚሆን ጠቁመዋል፡፡

እንዲሁም ተገልጋዮች አሮጌውን መታወቂያቸውን ለመቀየር ብለው ወደ ተቋሙ መሄድ አይጠበቅባቸውም ያሉት አቶ ጥጋቡ፤ ነገር ግን ለሌላ አገልግሎት በሚሄዱበት ወቅት ማስቀየር እንደሚችሉ አብራርተዋል፡፡ ይህ አዲስ የነዋሪነት መታወቂያ ከነባሩ መታወቂያ የሚለይባቸው በርካታ ይዘቶች ያሉት ሲሆን፤ የመታወቂያውን ትክክለኛነት በማንኛውም ቦታ ስካን በማድረግ ማረጋገጥ የሚቻል መሆኑንና የፋይዳ ቁጥርን ያካተተ መሆኑን አስረድተዋል ፡፡

በተጨማሪ ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ ሲገባ የኦንላይን አገልግሎት አማራጭ ያለውና የራሱን የሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ የሚቻል ሲሆን፤ መታወቂያውን ከመተግበሪያው ላይ በማውረድ መጠቀም እንደሚቻልም ተገልጿል፡፡ ስለሆነም አንድ ሰው የአዲስ አበባ ነዋሪ ከሆነ ተጨማሪ የፋይዳ መታወቂያ መያዝ አይጠበቅበትም ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ ምክንያቱም አዲሱ መታወቂያ የፋይዳ ቁጥሩን ያካተተ በመሆኑ ነው ብለዋል፡፡ ሲስተሙ የአገልግሎት ማነቆ የነበሩ ችግሮችን ሙሉ በሙሉ የሚቀርፍ ነው የተባለ ሲሆን፤ አዲሱ የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት ዲጂታል ሥርዓት በኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የበለጸገና ከኢሚግሬሽን፣ ከጤና፣ ከፍርድ ቤትና መሰል ተቋማት ጋር በቅንጅት የሚሠራ ስለመሆኑም ተጠቁሟል፡፡

CRRSA
የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ

## ርዕሰ -አንቀፅ

# አድዋ- የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ፋና እና የመልካም ዜጋ ተምሳሌት ነው!

የአድዋ ድል የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ተምሳሌት ብቻ አይደለም፤ የኢትዮጵያውያን የጸና የሥነ-ምግባር እሴት፣ የአንድነት እና ለመልካም ዜግነት የታላቅነት ማሳያም ነው። ይህ ድል በአውሮፓውያን ቅኝ ገዥዎች ላይ የተቀዳጀነው ወታደራዊ ድል ብቻ ሳይሆን፣ በወቅቱ የነበረው ትውልድ ለሀገራዊ ክብር የነበረውን ጥልቅ ታማኝነት እና ከራስ ጥቅም ይልቅ ለጋራ ህልውና የሰጠውን ዋጋ የሚያንጸባርቅ የሞራል ልዕልና ነው።

የአድዋ ጦርነት ሲታሰብ በግንባር ቀደምትነት የሚነሳው የኢትዮጵያውያን የመታመን እና ለሉዓላዊነት የመገዛት ስሜት ነው። አንድ መልካም ዜጋ ለሀገሩ ያለው ፍቅር ከግል ጥቅማጥቅም በላይ መሆን እንዳለበት አድዋ በተግባር አሳይቶናል። ሀገራዊ አንድነት የክልል (በወቅቱ በየአገር ግዛቱ) የግዛቱ መሪዎች የነበራቸውን ቅራኔ ወደ ጎን በመተው ለአንድ ዓላማ መቆማቸው፣ ብስለት የተሞላበት የመልካም ዜግነት መገለጫ ነው። ለቃል ኪዳን መታመን የውጫሌ ውል ሲጣስና የማታለል ተግባራት ሲሞከሩ፣ ኢትዮጵያውያን ያሳዩት ቁርጠኝነት "በሀቅና በእውነት" ላይ የተመሰረተ ዜግነትን ያረጋግጣል።

ሙስና በአጭር ትርጓሜው "የሕዝብን አደራ ለግል ጥቅም ማዋል" ነው። አድዋን ስንመለከት ግን የዚህ ተቃራኒ የሆነውን "ራስን ለሕዝብ አደራ አሳልፎ መስጠትን" እናያለን። የሀብት አጠቃቀምና ተጠያቂነት በዘመቻው ወቅት የነበረው ስንቅና ትጥቅ ያለ ብክነት ለዓላማው እንዲውል የተደረገው ቁጥጥር፣ ዛሬ ላለነው ዜጎች ለሕዝብ ሀብት ጥንቃቄ ማድረግን ያስተምራል። በሌላ በኩል ጠላት ሰላዮችንና ከሃዲዎችን በመጠቀም ድልን ለመቀዳጀት ቢሞክርም፣ ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸውና ለንጉሣቸው የነበራቸው ታማኝነት ለዘመናዊው የፀረ-ሙስና ትግል ትልቅ ስንቅ ነው። ድሉም የጥቂቶች ሳይሆን የመላው ሕዝብ ተሳትፎ ውጤት መሆኑና እኩል መጋራቱ፣ መልካም ዜግነት ፍትሃዊነትን እንደሚጠይቅ ያሳያል።

የአድዋ ድል በወረቀት ላይ የሰፈረ ታሪክ ብቻ ሳይሆን፣ ዛሬ ላለብን የሙስና እና የሥነ-ምግባር መላላት ፈውስ የሚሆን "የሞራል መሠረትና ምንጭ" ነው። ሙስናን ለመከላከል ሕግና ተቋማት ብቻ በቂ አይደሉም፤ እንደ አድዋ ጀግኖች ለሀገር የሚቆረቆር፣ በታማኝነት የሚያገለግልና አደራን የማይበላ መልካም ዜጋ መገንባት ይገባል። "አድዋ የጥቁር ሕዝቦች ድል ብቻ አይደለም፤ የሞራል የበላይነት የታየበት፣ የታማኝነትና የጽናት ተምሳሌትም ጭምር ነው።"ዛሬም የሙስናን ደመና ለመግፈፍ የአድዋን መንፈስ፣ ያንን የማይበገረውን ሥነ-ምግባርና ለሀገር የመታመን እሴት በልባችን ማሳደር ይኖርብናል። አድዋ የሚያስተምረን ታላቅ ቁምነገር ሙስናን መከላከል የሚቻለው በጠንካራ የሥነ-ምግባር ግንባታ መሆኑን ነው።

አንድ መልካም ዜጋ ለሀገሩና ለህሊናው የታመነ ከሆነ፣ ምንም ዓይነት ምድራዊ ጥቅም የሀገርን ሉዓላዊነትና ክብር እንዲደራደር አያደርገውም። የአድዋ መንፈስ ዛሬም ድረስ የሚነግረን "ለሀገር መታመን ከሁሉም በላይ ትርፋማ ነው" የሚለውን የማይደበዝዝ እውነት በመሆኑ ሁላችንም በሥነምገባር ግንባታና ሙስና መከላከል ለሀገራችን ታምነን መስራት እንዳለብን መልዕክት ማስተላለፍ እንወዳለን።

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀን የሚዘጋጅ ጋዜጣ

ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission
ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች
EARS

## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ሞባይል 0953222255
0953222299
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

NCRS

## ቆይታ

# ዲጂታል የሀብት ምዝገባ ሙስናን የሚከላከል ዘመናዊ መሳሪያ

*በፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን "ፀረ-ሙስና" በሚል ስያሜ የሚዘጋጅ፣ በወር ሁለት ጊዜ (በየ15 ቀኑ) የሚወጣ ጋዜጣ ነው። ይህ ጋዜጣ በሙስና መከላከል፣ ሥነ-ምግባር ግንባታ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ በተለያዩ አምዶች ይከፋፈላል።*

*ከነዚህ አምዶች መካከል "ቆይታ" የሚለው አምድ አንዱ ነው። ከአሁን በፊት በዚህ አምድ የተለያዩ እንግዶች ጋር ቆይታ ያደረግን ሲሆን፣ ዛሬም አንድ እንግዳ ይዘን መጥናል።*

በዚህ ዙሪያ የፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሀብት ምዝገባ ስራን ከወረቀት ወደ ዲጂታል በማሸጋገር የኢትዮጵያ የዲጅታል ሀብት ምዝገባ (Electronic Asset Registration System (EARS)) ሲስተምን በማስጀመር ትልቅ ለውጥ አድርጓል። ይህ ሲስተም ግልጽነትን፣ ተጠያቂነትን እና የሙስና መከላከልን ያጠናክራል። በዚህ ቃለ-መጠይቅ የሀብት ምዝገባ እና የጥቅም ግጭት ማስወገድ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር የሲስተሙን ጥቅሞች፣ ልዩነቶችና የወደፊት እቅዶችን ገልጸዋል። ከወ/ሮ ኮከብ አንበርብር ጋር የተደረገው ቆይታ እንደሚከተለው ቀርቧል። መልካም ንባብ!

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** የሀብት ምዝገባ ሂደት ከወረቀት ንክኪ ወደ ዲጂታል መሸጋገሩ ይታወቃል። ይህ አዲሱ የዲጂታል ሀብት ምዝገባ ሥርዓት ከድሮው አሰራር በምን ይለያል?

**ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር፡-** ኮሚሽኑ ቀደም ሲል የሀብት ምዝገባ ስራን በወረቀት(manual system) በመጠቀም ሲሰራ የቆየ ሲሆን፤ አሁን ላይ የዲጂታል ሀብት መመዝገቢያና ማሳወቂያ ሲስተም(EARS) በማስለማት የተቋማት ኃላፊዎችና ሰራተኞች የገቢ ምንጫቸውን በዲጂታል እንዲያስመዘግቡ እየሰራ ይገኛል። በማኑዋል የነበረው የሀብት ምዝገባ ስራ ጊዜ ይወስዳል፤ የሰነድ ማስቀመጫ ፋይልና ቦታ ይፈልጋል፤ የተሞሉ መረጃዎች ሊበላሹ ወይም ሊጠፉ ይችላሉ። የተመዝጋቢዎችንም መረጃ ለማደራጀት እና ሪፖርት ለመስራት አድካሚና ጊዜንም የሚጠይቅ ነው። የዲጂታል ሀብት ምዝገባ ሲስተም በማኑዋል የነበሩ ችግሮችን በመቅረፍ ተመዝጋቢዎች ባሉበት ሆነው በእጅ ስልካቸው ወይም በሌሎች አማራጮች ጊዜን በቆጠበ ሁኔታ መመዝገብ ይችላሉ። በቀላሉ መረጃዎችን ማደራጀትም ሆነ አስፈላጊውን ሪፖርት ለማውጣት ምቹ ነው፤ የመረጃዎች ደህንነትም የተጠበቀ እንዲሆን ያደርጋል።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** ዲጂታል ሀብት ምዝገባ ግልጽነትን በማረጋገጥ እና ሙስናን በመከላከል ረገድ ያለው ፋይዳ ምንድ ነው?


**ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር፡-** የሀብት ምዝገባ አተገባበርን ወደ ዲጂታል መቀየሩ የተመዝጋቢዎችን የሀብት መረጃ በተገቢው ሁኔታ በሲስተሙ ተጠብቆ ከመደራጀቱ በተጨማሪ ከእጅ ንክኪ በፀዳ መልኩ ስለሚሰራ የመረጃ መሰረዝ፣ መደለዝ እና የተሳሳተ መረጃ መሙላትን ይከለክላል።በሲስተሙ መረጃውን የሚያደራጁት ጥቂትና ኃላፊነት የተሰጣቸው ስለሆኑ የመረጃ ስህተትና ብክነት እንዳይኖር በማድረግ ተጠያቂነትን ያጠናክራል፤ የመረጃ መጠባበቂያ (backup) ስላለ መረጃ አይጠፋም። ከዚህ በተጨማሪ የሀብት ምዝገባ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በቀላሉ መጠቀምና ብልሹ አሰራሮችን መከላከል ያስችላል። በአጠቃላይ ዲጂታል የሀብት ምዝገባ ግልጽነትን ይጨምራል፤ ተጠያቂነትን ያጠናክራል፤ የሀብት መረጃን ትክክለኛነት ለመከታተል ቀላል በማድረግ ሙስናን ለመከላከል ይረዳል።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** አንድ ተመዝጋቢ በዲጂታል ሲስተሙ ላይ ያስመዘገበው ሀብት ትክክለኛ መሆኑን ኮሚሽኑ እንዴት ያረጋግጣል? ከሌሎች ተቋማት (ለምሳሌ ከባንኮች፣ ከመሬት አስተዳደር ወይም ከትራንስፖርት ባለስልጣን) ጋር ያላችሁ የዲጂታል መረጃት ትስስር ምን ይመስላል?

**ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር፡-** ኮሚሽኑ ተመዝጋቢው በዲጂታል ሲስተም ላይ ያስመዘገበው ሀብት ትክክለኛ መሆኑን በተለያዩ መንገዶች ያረጋግጣል። የተመዘገበውን ሀብት ከተለያዩ መረጃ ሰጪ ተቋማት ጋር ያለውን ንብረት መረጃ በማሰባሰብ፣ በማደራጀት እና በመተንተን የሀብት ምዝገባው ትክክለኛነት ይረጋገጣል። ለምሳሌ፡- ከባንኮች የባንክ ሂሳብ መጠን፣ ተቀማጭ ገንዘብ፣ የብድር መረጃ እና ያልተመዘገበ አካውንት ቁጥር ካለ፣ ከመሬት አስተዳደር ጋር በተያያዘ የመሬት ባለቤትነት፣ የቤት ወይም ንብረት መዝገብ፣ ከትራንስፖርት ባለስልጣን ደግሞ የመኪና ባለቤትነት፣ የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች እንዲሁም ከንግድ ቢሮዎች እንዲሁ አስፈላጊውን መረጃ በማሰባሰብ እና ከተመዘገበው ሀብት ጋር በማመሳከር የሀብት መረጃ ትክክለኛነት ይረጋገጣል። ልዩነት ካለው የሀብት ምንጩ እንዲረጋገጥ እና ሀሰተኛ መረጃ በመስጠትም ጭምር ተጠያቂ ይደረጋል። ከመረጃ ሰጪ ተቋማት ጋር መረጃዎችን በዲጂታል ቅብብሎሽ ይደረጋል።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በሕጉ መሠረት ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ተለይተው ሳለ ሳይመዘገቡ የቀሩ ወይም የተሳሳተ መረጃ የሰጡ አካላት ላይ ኮሚሽኑ ምን ዓይነት አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል?

**ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር፡-** በቅድሚያ ሀብትን ማስመዝገብ ሙስናን ለመከላከል ያለውን ጥቅም ግንዛቤ በመፍጠር እንዲመዘገቡ ክትትል ይደረጋል፤ በተቀመጠው ጊዜ ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ የመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል። በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲያስመዘግቡ ይጠየቃሉ። ይህ ካልሆነ በሀብት ማሳወቅና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 668/2002 መሠረት ተጠያቂ ይደረጋሉ፤ በዚሁ መሰረት እየተተገበረ ይገኛል።



*ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር የሀብት ምዝገባ እና የጥቅም ግጭት ማስወገድ መሪ ሥራ አስፈጻሚ*

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** እስካሁን ባለው ሂደት ምን ያህል የመንግሥት ተሿሚዎች እና ባለሙያዎች ሀብታቸውን በዲጂታል መንገድ አስመዝግበዋል? በዕቅዳችሁ መሠረት ሁሉንም ተገቢ አካላት ለማዳረስ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችስ አሉ?

**ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር፡-** በተግዳሮት ደረጃ የሚታዩት ከተለመደው የማኑዋል አሰራር ወደ ዲጂታል ለመቀየር ከቴክኖሎጂ አተገባበር ጋር የሚያጋጥም የክህሎት ክፍተት ነው። ይሀን ለመፍታት በተደጋጋሚ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡ ፡ ይህ የክህሎት ብቃት ወደፊት እያደገ የሚሄድ ነው። እስከአሁን በዲጂታል የሀብት ምዝገባ ሲስተም 42,617 ወንዶች 20,191 ሴቶች በድምሩ 62,808 ባለሙያዎችና የስራ ኃላፊዎች ሀብታቸውን አስመዝግበዋል።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** የዲጂታል ሀብት ምዝገባውን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ እና ወደፊት አርቲፊሻል ኢንተለጀንስን (AI) በመጠቀም ያልተገቡ የሀብት ክምችቶችን ለመለየት ያሰባችሁት አዲስ አሰራር አለ?

**ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር፡-** ኮሚሽኑ ያስለማው የዲጂታል ሀብት ምዝገባ ሲስተም(EARS) በቀጣይ እየተሻሻለና እያደገ የሚሄድ ነው። በትክክል ያልተመዘገበ የሀብት መረጃን ወይም የተደበቀ የሀብት መረጃን በቀላሉ በማጣራትና በማረጋገጥ ምንጩ ያልታወቀ የሀብት ክምችትን በመከላከል የግልጽነትና የተጠያቂነት አሰራርን ለማጠናከር በቀጣይ እንደሀገር ከሀብት መረጃ ሰጪ ተቋማት ጋር የተጠናከረ የዲጂታል አሰራርን መዘርጋት ያስፈልጋል።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** መልዕክት ወይም ቀረ የሚሉት ካለ?

**ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር፡-** የዲጂታል የሀብት ምዝገባ ስራ ሙስናን ለመከላከል በጣም ጠቃሚ ዘመናዊ አሰራር ነው። ዋና ዓላማው በተሻሻለው የኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 እና በሀብት ማሳወቅና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 668/2002 መሠረት በመንግስት ተቋማት፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚገኙ አመራሮች እና ሠራተኞች ሀብታቸውን እና የገቢ ምንጫቸውን ሲያስመዘግቡ የተለመደውን የማኑዋል/ የወረቀት አሰራር በማስቀረት በተቀላጠፈ አሰራር ማካሄድ ነው።

ይህም የመረጃ ደህንነትን በመጠበቅ፣ የጊዜ እና ሀብት ብክነትን በመቀነስ፣ የግልጽነት አሰራርን በማሳደግ፣ በህገ-ወጥ መንገድ አላግባብ የሚከማች ሀብት እንዳይኖር በመከላከል፣ የተጠያቂነት አሰራርን በመዘርጋት እና በተቋማት ላይ የህዝብ አመኔታን በማሳደግ ብልሹ አሰራሮችንና ሙስናን መከላከል ያስችላል።

# ሳይቃጠል በቅጠል

## “የፖሊስ አገልግሎት ዲጂታላይዜሽን ለሙስና ስጋቶች የቴክኖሎጂ ምላሽ”



የአማራ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ተቋማዊ ሪፎርሙን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር በወሰደው እርምጃ፣ በቅርቡ የዲጂታል መታወቂያ አሰራርን በይፋ ስራ ላይ አውሏል። ይህ እርምጃ ተቋሙን ከማዘመን ባለፈ፣ ለዘመናት የፖሊስን ስም ሲያጠፉና የህዝብን አመኔታ ሲሸረሽሩ የቆዩ የሙስና እና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በዘላቂነት ለመቅረፍ እንደ ዋነኛ ስትራቴጂ ተወስዷል።

**የቴክኖሎጂ እጥረት የፈጠራቸው የሙስና ተሞክሮዎች**

የዲጂታል አሰራር ከመዘርጋቱ በፊት የነበረው የወረቀት መታወቂያ አሰራር፣ ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ በርካታ ክፍተቶችን ፈጥሮ ቆይቷል። ቀደም ሲል ይስተዋሉ የነበሩ ዋና ዋና ችግሮችን መለስ ብለን ስንመለከት፦

ሀሰተኛ መታወቂያዎች፦ በቀላሉ ሊባዙና ሊሰረዙ የሚችሉ በመሆናቸው፣ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ግለሰቦች የፖሊስን መለዮና ሀሰተኛ መታወቂያ በመጠቀም ህዝብን ለብዝበዛ ሲዳርጉ ቆይተዋል። ዜጎች የሚገጥማቸው ሀሰተኛ መረጃ በመያዝ ፖሊስ በመምሰል የሚያጭበረብር አካል “ትክክለኛ ፖሊስ” መሆኑን የሚያረጋግጡበት ፈጣን ዘዴ ባለመኖሩ፣ በየመንገዱና በየሰፈሩ ለማጭበርበርና ለዝርፊያ ሲጋለጡ ቆይተዋል።

ከስራ የተሰናበቱ አባላት፦ ከተባረሩ በኋላ በመታወቂያቸው ወንጀል መስራት፣ በዲሲፕሊን ጉድለት ወይም በወንጀል ተጠርጥረው ከስራ የተሰናበቱ አባላት፣ የያዙትን የወረቀት መታወቂያ ሳይመልሱ በመቅረት የቀድሞ ስልጣናቸውን ለህገ-ወጥ ስራ ሲጠቀሙበት ቆይተዋል። ይህም “ከስራ የወጣ ፖሊስ ዛሬም በፖሊስ ስም ህዝብን ያጉላላል” የሚል መራር ቅሬታ ሲያስነሳ ነበር።

የመረጃ ቋት አለመኖርና የተጠያቂነት መጥፋት፦ የአባላት መረጃ በማዕከላዊ የመረጃ ቋት (Database) ባለመያዙ፣ አንድ አባል በአንድ አካባቢ ሙስና ፈጽሞ ሲባረር፣ ሌላ የክልሉ ዞን ወይም ወረዳ ሄዶ አዲስ መታወቂያ አውጥቶ ስራ የሚጀምርበት አጋጣሚ ነበር። ይህ “የመረጃ መቆራረጥ” የሙስና ሰንሰለቱ እንዳይበጠስ አድርጎታል።

**የዲጂታል መታወቂያው ቴክኖሎጂያዊ ምላሽ**

ይህ አዲስ የቴክኖሎጂ ስምሪት በፖሊስ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን በመድፈን፣ ተቋሙን ከሙስና የጸዳ ለማድረግ እንደ ዋና መሳሪያ እየታየ ይገኛል። የቴክኖሎጂው ዋና ዋና ፋይዳዎች የሚከተሉት ናቸው።

የማይተካ ማንነት (QR Code)፦ እያንዳንዱ መታወቂያ በውስጡ የያዘው ፈጣን ምላሽ (QR Code) የፖሊስ አባሉን ትክክለኛነት በሰከንዶች ውስጥ ያረጋግጣል። ማንኛውም ተቆጣጣሪ አካል ወይም ዜጋ በስልኩ ኮዱን በማንበብ የግለሰቡን ስም፣ ማዕረግና የስራ ድርሻ ማረጋገጥ ይችላል። ይህ “መለዮ ለብሰው” ህገ-ወጥ ክፍያ የሚጠይቁ ደላሎችንና ሀሰተኛ ፖሊሶችን ሙሉ በሙሉ ከጨዋታ ውጭ ያደርጋቸዋል።

ቅጽበታዊ ቁጥጥርና ዕገዳ፦ አዲሱ አሰራር ከሰው ኃይል አስተዳደር ጋር የተቆራኘ ነው። አንድ የፖሊስ አባል ከስራ ሲሰናበት ወይም በዲሲፕሊን ጉድለት ሲታገድ፣ መታወቂያው በሲስተም ደረጃ ወዲያውኑ አገልግሎት እንዳይሰጥ ይደረጋል። ይህም ግለሰቡ መታወቂያውን በአካል ባይመልስ እንኳ፣ በየትኛውም ቦታ ሊያጭበረብር የሚችልበትን ዕድል ይዘጋል።

የመረጃ ትክክለኛነትና ተጠያቂነት፦ የአንድ አባል ሙሉ ታሪክ በማዕከላዊ የመረጃ ቋት ስለሚመዘገብ፣ ማንነቱን ደብቆ ለሙስና የሚጋለጥ አባልን በቀላሉ ለመቆጣጠርና አስፈላጊውን ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ ያስችላል።

**ለፍትሃዊ አገልግሎት አዲስ ምዕራፍ**

ፖሊስ ራሱን በቴክኖሎጂ ማዘመኑ ከህብረተሰቡ ጋር ያለውን ግንኙነት ግልጽና ተዓማኒ ያደርገዋል። ዜጎች የሚገጥማቸው ፖሊስ ትክክለኛ መሆኑን በተረዱ ቁጥር፣ ያልተገባ ክፍያ ከመፈጸም ይልቅ በህግ አግባብ መስተናገድን ይመርጣሉ። ይህም በፖሊስና በህዝብ መካከል ያለውን “የጥቅም ትስስር” በመበጠስ ለፍትሃዊ አገልግሎት መንገድ ይከፍታል።

ይህ የዲጂታል መታወቂያ ዝርጋታ የአማራ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ሙስናን ለመታገል የገባውን ቃል በተግባር እያሳየ መሆኑን ማረጋገጫ ነው። ቴክኖሎጂው የግለሰቦችን ፍላጎት በስርዓት በመተካት፣ ተቋሙን የህግ የበላይነት የሚከበርበትና የህዝብ አመኔታ ያተረፈ እንዲሆን ያደርገዋል። የአማራ ክልል የጀመረው ስራ ለሌሎች የክልል ፖሊሶች “ዲጂታል አብዮት” (Digital Revolution) የመንገድ ጠራጊ ነው። ይህ ተሞክሮ ወደ ሌሎች ክልሎች ሲሰፋ፣ ኢትዮጵያ በቴክኖሎጂ የታገዘ፣ ከሙስና የጸዳና ሥነምግባራዊ የሆነ የጸጥታ ኃይል እንዲኖራት ስለሚያደርግ በስፋት መስራትን ይጠይቃል።

## ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

በዚህ አምድ የተለያዩ ከሙስና እና ብልሹ አሠራር ጋር በተያያዘ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከናወኑና ለህብረተሰቡ ከፍተኛ እውቀትና እውነተኛ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የሚታመኑና በሙስና ወንጀል የተመዘበረ የሀገር፣ የህዝብና የመንግስት ሀብት በማስመለስ ዙሪያ የተከናወኑ ተግባራት እና ግንዛቤ የሚፈጥሩ ዋና ዋና ጉዳዮች አጠር ተደርገው የሚቀርቡበት ነው፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 5ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት በጥቅም በመመሳጠር መንግሥትን ከ120 ሚሊየን ብር በላይ ያሳጡ ተጠርጣሪዎች ላይ ክስ መስርቷል፡፡ ተከሳሾቹ በጉምሩክ ኮሚሽን የደወሌ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ሠራተኛ የሆኑት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በደወሌ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ አስተባባሪ እና የስካኒንግ ማሽን ምስል ትንተና ባለሙያ ሆነው ተመድበው ይሰሩ ነበር፡፡ በዚህ ወቅትም ከ3ኛ ተከሳሽ ጋር በጥቅም በመመሳጠር ታሕሳስ 21 ቀን 2018 ዓ.ም በ3ኛ ተከሳሽ አስመጪነት 595 የልብስ ማጠቢያ በሚል ሰነድ ከጂቡቲ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ 2 ሺህ 229 ቴሌቪዥኖች በስካኒንግ ማሽን ዕቃዎቹ ዝርዝር ፍተሻ ሳይደረግ በስካኒንግ ማሽን ተፈትሿል በሚል



የማረጋገጫ ማሕተም በመምታት ጭምር በልብስ ማጠቢያ ማሽን ስም ቴሌቪዥኖቹ እንዲያልፉ ማድረጋቸው ተጠቅሶ በየተሳትፎ ደረጃቸው መከሰሳቸው ተመላክቷል፡፡በ3ኛ ተከሳሽ ላይ ብቻ የቀረበው 2ኛ ክስ ደግሞ በሕጋዊ ሽፋን ምንም አይነት ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለባቸውን ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት በማሰብ በዲክላራሲዮን የተመዘገበው የልብስ ማጣቢያ ማሽን ነው በሚል 2 ሺህ 229 ቴሌቪዥኖች አስገብቶ ተገኝቷል የሚል ነው፡፡ በዚህም ለመንግሥት መክፈል የነበረበትን ከ125 ሚሊየን ብር በላይ ታክስ እና ቀረጥ በማሳጣት በመንግሥት ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ የጉሙሩክ ማጭበርበር ወንጀል ክስ ተመስርቶበታል፡፡ ተከሳሾቹ ተዘጋጅተው በክሱ ላይ ለመቅረብ በጠየቁት ተለዋጭ ቀጠሮ መሰረት በይደር መቀጠሩን ተዘግቧል፡፡

የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካልዎት NCRS ሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም ባሉበት ሆነው ይጠቁሙ!

## መልካም ዜጋ

### ከሚያሽከረክረው ባጃጅ ላይ ብዛት ያለው ብር ያገኘው ወጣት በታማኝነት ለፖሊስ አስረከበ

የሰሌዳ ቁጥር 01926 ሐረር የሆነችው ቲ.ቪ.ኤስ ባጃጅ አሽከርካሪ ወጣት ማቲዮስ ጎኔ በሐረሪ ክልል ጅኔላ ወረዳ በልዩ ስሙ ከፋሚሊ ሆቴል ወደ ቂሌ አካባቢ ኮንትራት ለማድረስ በመስማማት ተሳፋሪዎቹን ጭኖ ያደርሳል፡፡ ወጣቱ ሲመለስ ሌላ ተሳፋሪ በመጫን ሲንቀሳቀስ ከኋላ በፌስታል የተጠቀለለ ነገር በመመልከቱ ሲያጣራ ብዛት ያለው ብር ይመለከታል በዚህም የግል ጥቅሙን ሳያስቀድም በታማኝነት ቀጥታ ወደ ፖሊስ ኮሚሽን በመምጣት





አስረክቧል፡፡

የተገኘውን ብርም የሐረሪ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር አህመድ አብዲ በተገኙበት ለወንጀል ምርመራ ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ያህያ አብዱሰላም አስረክበዋል፡፡ የሌሴቅ ባጃጅ ማህበር ከዚህ በፊትም በማህበሩ አባላት ጠፍተው የሚገኙ የብርና ልዩ ልዩ ኤሌክትሮኒክሶችን ለፖሊስ ከማስረከብ ባሻገር በልማታዊ ስራዎችም ንቁ ተሳትፎ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ወጣቱ ላሳየዉ ታማኝነት የሐረሪ ፖሊስ ኮሚሽን ምስጋና አቅርቧል፡፡

# ኪነ-ጥበብ

## እጅ እየታመነ!

እምነት ከአለም ጠፋ ውለታም ባከነ፣
የሰው ሀይማኖቱ ገንዘብ ብቻ ሆነ፣
እግር ተረሳና እጅ እየታመነ፣
ፈጣሪ ሲሰራው ከሁሉም አልቆ፣
እንዲኖር ነበረ ህግና ስዓቱን እምነቱ ጠብቆ፡፡
እንዲህ ሆኖ ሳለ ማገልገል በምግባር፣
መሸጥ ባህል ሆነ ፍትህን በዲናር፣
ለህዝብ የተገባው ቃልኪዳን ተረስቶ፣
እጅ እየቀደመ እግር መሄድ ትቶ፡፡
የበሬን ውለታ ይባል ነበር ዱሮ፣
እጅ እግርን ቀደመ ከፈረስ ተምሮ፣
ሁሉም በእግር ይጓዝ በእጅ መሄድ ይበቃ፣
ምንጣፉም ይቀየር ያደፈው በጭቃ፡፡
ዝጋጃው ይነሳ ይጠርግ መንገዱ፣
ገንዘብ ለሌላቸው በእግር ለሚሄዱ፣
ይቀየር አቅጣጫው ክፍት ይሁን መንገዱ፡፡
ጨዋታው ይቀየር ሜዳው ይበል ሰፋ፣
ጎሉን ለማስቆጠር ሁሉም በእግሩ ይልፋ፡፡
እስከመቼ ሊኖር በእጅ እየተሄደ፣
ህሊና ተሸጦ ሆድ እየፈረደ፣
ታማኙ ተረስቶ ብልጥ እየነገደ፣
የሌቦች መግባቢያ ቋንቋውም ይወገድ፣
የሚሉት ይወገዝ ትንሽ መላ ውረድ፣
ከእንግዲህ ይበቃል በዚህ መሸዋወድ፣
አቀባይ ተቀባይ ሁሉም ይቅረብ ለፍርድ፡፡
‹‹ሲሾም ያልበላ ሰው ሲሻር ይቆጨዋል››፣
ሲባል የነበረው ያ ክፉ ሥነ-ቃል፣
ይሰረዝ ከመዝገብ ከእንግዲህ ያበቃል፡፡
ግንዛቤው ይስፋ ይሰበክ ትምህርቱ፣
ፍትህን ያስቀድም ሁሉም ለመብቱ፡፡